ቀን[Februari 19 2017

አምስተርዳም

# በአውሮፓ ለግዚያዊ ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች የቀረበ ግልጽ ጥያቄ

የፕሮፌሰር መራራ ጉዲናን በግፍ መታሰር አስመለከቶ በኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ ግፈኛ መንግስት የታሰሩትን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ በወያኔ መንግስት ላይ ጫና እንዲያደርጉ በአውሮፓ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በጋራ በቤልጅየም ብራስልስ በአውሮፓ ፓርላማ ጽ/ቤት ፊት ለፊት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በአውሮፓ በተለያየ ሃገር የምንኖር ኢትዮጵያኖች ግዚያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በማቋቋም አውሮፓ አቀፍ የጋራ ኮሜቴ እንዲመሰረት መደረጉ ይታወቃል። ይህም ኮሚቴ በተለያየ ግዚ የቴሌ ኮንፍራስ በማድረግ በመጨረሻ ለሰላማዊው ሠልፍ ሀጋዊ ፍቃድ እንዲያስፈቅድ ለቤልጅግ አስተባባሪ ኮሜቴ ሃላፊነት ሰጥቶ ቀኑን እንዲያሳውቅ መወሰኑ ይታወሳል።

የቤልጅግ አስተባባሪ ኮሜቴም የተሰጠውን የስራ ድርሻ በመወጣት ለ February 16 2017 ፍቃድ ማግኘቱን በማሳወቁ በየ ሃገሩ ያሉ ኮሜቴዎች ፍላየር እንዲበትኑና ቅስቀሳ በየሶሻል ሜድያ ተደርጎ የተጠናከረ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ለ February 16 2017 ብራሰልስ እንዲደረግ መወሰኑ ይታወቃል።በዚህም መስረት እኔ የምኖርበት የሆላንድ የኢትዮጵያ ማህበር ፍላየር አውጥቶ ለተጓዥች አውቶቢስ ምዝገባም አጠናቆም ነበር፡እኔም በፓለቶክ ክፍሎች እየገባሁ ቀስቅሻለሁ።ጉዞው 3 ቀን ሲቀረው ከቤልጅግ አስተባባሪ ኮሜቴ ለየሀገሩ በተላከው አስቸኳይ ኢሜይል ሰላማዊው የተቃውሞ ሰልፍ ላልተወሰነ ቀን መተላለፉን በማሳወቅ የተላለፈበትም ምክንያት ከፍቃድ ሰጭው አካል በተለይም ፓሊስ ለ 2 ሳምንታት በቦታው ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳይደረግ በመከልከሉ  ምክናያት እንደሆነ ተገልፆልናል በሜል ነበር። በዚህ መሰረት በሆላንድ የኢትዮጵያ ማህበርም ሰልፉ ለ April 6 2017 መተላለፉን የተላለፈበትን ምክንያት ከቤልጅግ አስተባባሪ ኮሜቴ የተላከውን ኤሜይል አባሪ በማድርግ ለአባላቱና ለመሄድ ለተመዘገቡት አስታውቋል፤ እኔም ቀድም ብዩ በተናግርኩባቸው ፓልቶክ ክፍሎች ሰላማዊ ሰልፉ ላልተወሰነ ግዜ መተላለፉን ከይቅርታ ጋር አሰርድቻለሁ። በሁኔታው ግራ የተጋቡት ወገኖች ጉዳዩ ሰለከነከናቸው በተለይም የወቅታዊ የኢትዮጵያ መወያያ ፓልቶክ ክፍል (Ethiopian current Affairs Discussion Room)  የቤልጅግ አስተባባሪ አባል የሆኑትን አቶ ኢጋዝን በመጋበዝ ሰላማዊ የተቃውሞ ስልፍ በምን ምክንያት እንደተሰረዘ እንዲያስረዷቸው ጥያቄ ያቀርባሉ፤ አቶ ኢጋዝም ሰላማዊ ስልፍ እንደሚካሂድና የአውሮፓ ምክር ቤትም የሰጠውን ፍቃድ እንዳልሰረዘ ይገልፃሉ። በተባለው ቀንም አቶ ኢጋዝን ጨምሮ ከ 20 ያነሱ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያኖች በቦታው በመገኘት ተቃውሟቸውን አስምተውል።

## ለአውሮፓ ግዚያዊ ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች በተለይም ለቤልጅግ ኮምቴ የማቀርበው ግልጽ ጥያቄ ፤

1- ለብዙ ግዜ የተደከመበት ሰላማዊ ሰልፍ ያለ በቂ ማስረጃ ለመሰረዝ ምክንያታችሁ ምንድነው?

2- ለሰላማዊው ሰልፍ መስረዝ ፍፁም ሃላፊነት በጎደለው የሰጣችሁት የተሳሳተ መረጃ ምንጩስ ከየት የተገኘ ነው?

3- በወቅቱ በአስተባባሪው ኮሚቴ ቴሌ ኮንፍራንስ በአፅኖት የተነጋገርንበት ሁኔታ የዚህ ኮሜቴ ዋናው አላማ ይህን ሰላማዊ ሰልፍ ለማስተባበር ከዚህ በፊት ይታይ የነበረው አጓጉል መጓተትና አላስፈላጊ የድርጅት ክፍፍል እንድይኖር በመሪ አላማው ፕሮፌሰር መራራ እና ሁሉም የፓለቲካና የህሊና እስረኞች ይፈቱ የሚል ብቻ እንድሆን የተወሰን ነበር፤ለምን ተገባሪያዊ አልሆነም?

4- በእሁዱ የመጨረሻ ቴሌ ኮንፍራንስ ለምን እኔ እንድገኝ አልተፈለገም?

5- ይህንን ህዝብን ጥርጣሪ ውስጥ የከተተውን ጉዳይ ወደፊት ለምናደርገው የጋራ ትግልና አብሮ ለመስራት ትልቅ ክፍተት ሊፍጥር እንደሚችል እየታወቀ ለምን ተደባብሶ እንዲታለፍ ተፈለገ?

6-የቤልጅግ አስተባባሪዎች በማህላችሁ የተፈጠረው ልዩነትና የላካችሁት የተሳሳት መረጃ የተደከመበትን ስራ ሁሉ ያለ ዋጋ ያስቀረና ተጠያቂነትንም ያስከተለ በመሆኑ ከህዝብ ለሚቀርበላችሁ ጥያቄ ለመምለስ ዝግጅ ናችሁ ወይ?

ማጠቃልያ፤ ከዚህ በላይ በዝርዝር ሀሳቤን ለመግለፅና ጥያቄ በግልፅ ለማቅረብ የተገደድኩት ለኔም አዲስ የሆነና በቅዳሜ ለት(Ethiopian current Affairs Discussion Room) ውስጥ በተደረገው ውይይት ጥያቄ በቀረበልኝ ግዜ በውቅቱ በሰላማዊ ሰልፉ ላይ የነበሩ ወገኖች ቅሪታቸውን በመግለጻቸው ነበር። እኔም አቶ ኢጋዝ (Ethiopian current Affairs Discussion Room) ቀርበው ሲጠየቁ በቦታው ያልነብርኩና ያልሰማሁ መሆኑን ሰላማዊው ስልፍ መስረዙን እንጂ መካሄዱን ገና መስማቴን እንደዚህ አይነት ድርጊት ከተፈፀመ እኔም አቶ ኢጋዝም ያልንብት ኮሜቴ በግልጽ መልስ መስጠት እንዳለበት በማስረድት ለመመለስ ሞክሪያለሁ።ይህንንም ፅሁፍ በግልፅ ለመፃፍ ያስገደደኝ አሕጉራዊ የህዝብ ጥያቄ በአስቸኳይ ምላሽ መሰጠት አለበት ብዬ ሰላመንኩብት ነው፤የአውሮፓ ኮምቴና በተለይም የቤልጅግ ኮሜቴ የጉዳዩን አሳሳቢነትና የተጣለበትን ሃላፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት በአጭር ቀን ውስጥ መልስ እንዲሰጥበት በአክብሮት አሳስባለሁ።

ማሳሰቢያ፤ ለግንዛቤ ስብሰባው የተጠራበትን የሆላንድ ፍላየርና ስብሰባው ስለመቅረቱ ከቤልጅግ ኮምኒቲ የትላከውን ኤሜይል መልክት አብሪ አያይዢዋለሁ።

ኢተዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር !!!

ከሰላምታ ጋር !

ወንደሰን ገ/ሕይወት(ከሆላንድ ኮምቴዎች አንዱ

From: **Ethiopian Community in Belgium** <ethiopian.community@gmail.com>
Date: 2017-02-13 11:51 GMT+01:00
Subject: {Ethiopian Forum} Message from The Organising Committee of the upcoming Demonstration
To: ethiobelgium <EthioBelgium@googlegroups.com>

ለመላው በአውሮፓ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ !!
በ ፊቡራሪ 15/2017 በሹማን ብራስልስ ሰልፍ ለመሳተፍ የተዘጋጃችሁ ወንድሞችና እህቶች በሙሉ። አሁን ዘግይቶ በደረሰን የብራስልስ ፖሊስ መልዕክት እና የአካባቢዝ አስተዳደር ከፊታችን ማክሰኞ ጀምሮ እስከ ፊታችን እሁድ ድረስ ሊዘልቅ የሚችል የፖሊሳዊ ስራ ምክናየት ባካባቢው የሚካሄድ ማንኛውንም እንቅስቃሴ አግደዋል።

ስለዚህም የሰላማዊ ስልፋችንን ቀን እንድንቀይር ተገደናል።

በመሆኑም ከኮሚቴዎች ጋር ተነጋግረን በበለጠና በተጠናከረ ዝግጅት ለ አፕሪል 6/2017 ከ 13 ሰዓት ጀምሮ ማድረግ እንደምንችል ስለተገለጸልን መልዕክታችንን ከታላቅ ይቅርታ ጋር እናስተላልፋለን።




የኢትዮጵያ ኮሚውኒቲ በቤልጂየም